# መንፈሳዊ ፍርድ እ.ኤ.አ በግንቦት 21/2011ዓ.ም ጀምሯል ፡፡

## በፍርድ ቀን ውስጥ መኖር በራሪ ጽሁፍ ተከታታይ ቁጥር 1

እ.ኤ.አ.ግንቦት 21,2011ዓ.ም በዓለም ከዚህ በፊት ሆኖ ከነበረው ይልቅ ለህዝብ የተስተዋወቀ ቀን ነበር፡፡ይህም በማስታወቂያ መለጠፊያ ቢልቦረዶች፣እንዲሁም በአውቶቢሶች ላይ ማስታወቂያ በመለጠፍ ለህዝብ ይፋ ሆኖ ነበር፡፡ መልዕክቱ፤በተሽከርካሪዎች፤ላይ፤በሚለጠፉ፤ወረቀቶች፣ በቲሸርቶች፣በጽሁፎች፣በመጽሄቶችና በጋዜጦች ላይ ይታይ ነበር፡፡ቀኑ የፍርድ ቀን እንደሚሆን ፣አብዛኛው የዓለም የመጨረሻው የእግዚአብሔር ፍርድ እንደሆነ አድርጎ በመያዝ በተሰባሰበ ትንፋሽ በመጠባበቅ ላይ ይገኝ እንደነበር በዓለም ላይ የሚገኙ የህዝብ የዜና መገናኛዎች የወንጌሉን መልእክት አስተጋብተዋል ፡፡

ይሁንና፣ ምንም ነገር አልሆነም (መስሏል) ፡፡ ነገሮች እንደታሰበው አልመጡም ፡፡ከግንቦት 21/2011 ዓ.ም እ.ኤ.አ. ቀን ጋር አብረው የሚሄዱ ምንም ዓይነት ዓለምአቀፋዊ የምድር መንቀጥቀጥና አስፈሪ የሆኑ ነገሮች አልነበሩም ፡፡ በምትኩ ያ ቀን ልክ እንደሌላው እንደማንኛውም ቀን መጥቶ አልፏል ፡፡ በአጠቃላይ ውጫዊ በሆነ ሁኔታ ሊታይ የሚችል ምንም ነገር አልነበርም፡፡ በዓለም ውስጥ ያሉ በረካቶች፣ እንደገና እየኖሩ ሲሆን ፣አጠቃላዩን አስተሳሰብም መሳለቂያ አድርገዋል ፡፡ «አዩ» «ይህ በአጠቃላይ ሞኝነት ነበር» በማለት ተናግረዋል ፡፡ ደግሞም እነርሱ ብቻ ሳይሆኑ እነዚያ በአብያተክርስቲያናት የሚኖሩት በተመሳሳይ በመደሰት ፤«ቀኑን እና ሰዓቲቱን ማንም ሰው ሊያውቅ እንደማይችል ነግረናችኋል! »በማለት ተናግረዋል ፡፡

ሆኖምግን፣ዓለምና ቤተክርስቲያን ኃላፊነትን/ተጠያቂነትን ለመውሰድ ወድቀውበት የነበረው እነርሱ እንዲያልፉበት መንፈሳዊውን ፍርድ ለማምጣት የእግዚአብሔር ዝንባሌ መሆኑ ነበር፡፡ መንፋሳዊ የሆነው ፍርድ ፣ ሊታይ የማይቻል እንደማንኛውም መንፈሳዊ ነገር ፣አንድ መንፈሳዊ የሆነ ነገር ነው ፡፡ በአተረጓጎም ለሰው ዓይን የማይታይ የሆነ አንድ ነገር ማለት ነው ፡፡ ለምሳሌ ፣እግዚአብሄር መንፈስ እንደሆነ መጽሐፍቅዱስ ይገልጻል ፡፡

*«እግዚአብሔር መንፈስ ነው፥ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል፡፡»(ዮሐንስ 4፣24)*፡፡

እግዚአብሔር መንፈሳዊ ህልውና ያለው እንደሆነ መጽሐፍቅዱስ ይነግረናል ፡፡ ነገርግን ዓለም እርሱን ሊያየው የማይችል ስለሆነ ፣አና ሊዳስሰውም ስለማይችል ፣እንዲሁም ደግሞ በዚህ ስሜት እርሱን ሊመረመሩት የማይቻላቸው ስለሆነ ፣ስለዚህ በዓለም ምክንያታዊነት አንጻር እግዚአብሔር በህልውና የሚኖር አይደለም ፡፡ መንፈሳዊ ነገሮች በቀላሉ ለዓለም ምንም ህልውና የላቸውም ፡፡ ነግርግን ፣በእርግጥ እግዚአብሄር ህያው ነው ፡፡ ምንም እንኳን ፣በፍጥረታዊ ዓይን ሊታይ አለመቻሉ ሀቅ ቢሆንም ፣ እርሱ አሁንም በጣም እውነት ነው ፡፡ የእግዚአብሄር ህዝቦች ይህንን ሊረዱት ይችላሉ ፡፡ እኛ ደግሞ መጽሐፍቅዱስ መንፈሳዊ መጽሐፍ መሆኑንም እንረዳዋለን ፡፡ እርሱ የእግዚአብሄር መጽሐፍ ሲሆን ፣ደግሞም መንፈሳዊም ስለሆነ፣ መጽሐፍቅዱስ ሙሉ በመሉ መንፈሳዊ እውነት በመሆኑ እኛ በአጠቃላይ የሚገርመን አንሆንም ፡፡

የእግዚአብሄር ህዝቦች በእምነት ዓይኖች በኩል መንፈሳዊ የሆኑት/የማይታዩት ነገሮች/ ለአማኝ የሚታዩ እንደሆኑ ያምናሉ ፡፡

*«እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ፥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው፡፡» (ዕብራውያን 11፣1)* ፡፡

እርሱን ሊያዩት ባለመቻላቸው ምክንያት አብዛኛው ዓለም የእግዚአብሄርን ህልውና የሚክዱ ስለሆኑ፣ መንፈሳዊ/የማይታይ/ የእግዚአብሄር ፍርድ የሚለው አስተሳሰብ ለእነርሱ ቂልነት ቢመስላቸው አይገርመንም፡፡ ይሁንና እንደ መጽሐፍቅዱስ አማኞች እኛ በአውነቱ ዓለም በአጠቃላይ ያንን እንደሞኝነት ወይም ቂልነት አድርጎ እንዲያገኙት አንፈልግም ወይም አናስብም ፡፡

የእኛ የመጀመሪያው ወንጌላችን፣የመጀመሪያው መጽሐፍ መጽሐፍቅዱሳችን፣የመጀመሪያው አዳኛችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዓለም ዘንድ ሞኝነት ተደርጎ መታሰቡ፣የእግዚአብሄር ልጅነትን ከመጠራጠር ባለፈ መንፈሳዊ ነገሮችን በሚመለከት ዓለም እጅግ ከመጠን በላይ የታወረና ግድለሽ መሆኑን የሚሳይ ነው ፡፡

እናም መንፈሳዊ በሆኑት ነገሮች ሁሉ መመሪያችንን ወይም አቅጣጫችንን ከዓለም አንወስድም፡፡ለእኛ እና ለእምነታችን ዓለም ያለው አመለካከት ለእግዚአብሄር ልጆች በፍጹም ጠቀሜታ የለውም፡፡ አይደለም ፡፡ እኛ እንደ አንድ የእግዚአብሄር ልጅ ብቸኛው ሀሳባችን የሚሆነው መጽሐፍቅዱስ ምን ይላል የሚለው ነው ፡፡

መልካም ፣ያንን ጥያቄ እንጠይቅ ፣ መንፈሳዊ የፍርድ ቀን ስለሚለው አስተሳብ የእግዚአብሄር ቃል ምን ይላል? ይህ የሚቻል ነውን? ለእንደዚህ ዓይነቱ አስተሳሰብ መጽሐፍቅዱሳዊ የሆነ ቀደም ሲል የተፈጸመ ክስተት ይኖራልን? እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ይቻል ዘንድ ለመልሶቹ መጽሐፍቅዱስን መመርመር ይገባናል፡፡ እንደዚሁም ደግሞ እንደዚያ ስናደርግ ይህንን የመጀመሪያ ነጥብ በሚመለከት እንደዚያ የተከሰቱ በፍጹም መልካም በሆነ ሁኔታ የሚስማሙ መረጃን እናገኛለን ፡፡

## የመጀመሪያው ፍርድ በኤደን ገነት፤መንፈሳዊ ፍርድ

ምርመራችንን በዘፍጥረት መጽሐፍ እንጀምር ፡፡ አዳም ከተፈጠረ በኋላ ወዲያውኑ በኤደን ገነት ውስጥ ከሚገኙት ዛፎች መካከል አንዱን በሚመለከት እግዚአብሄር በጣም ጥብቅ የሆነ ማስጠንቀቂያን ሰጥቶታል ፡፡

*«እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፡፡ ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፤ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና፡፡ » (ዘፍጥረት፣16-17)*

ትልቅ በርካታ የሆነ ህዝብ ፣ይልቁንም ከመጽሐፍቅዱስ ጋር ምንም ትውውቅ የሌላቸው በርካታ ሰዎች ፣ አዲስ ለተፈጠረው ሰው ይህ የመጀመሪያው ብቸኛ ህግ እንደተሰጠው ለመስማታቸው ምንም ጥርጥር የለውም ፡፡እግዚአብሄር ለሰው በግልፅ ከዚያ ልዩ ከሆነ ዛፍ ፍሬ እንዳይበላ ነግሮታል ፡፡ እንዲሁም ደግሞ እግዚአብሄር ለሰው በእርግጥ ከዚያ ዛፍ ፍሬን በበላበት ቀን በእርግጥ ሞትን እንደሚሞት ነግሮታል ፡፡ ይህ በጣም ቀጥተኛ የነበረ፣አጠራጣሪ ያልሆነ አነጋገር ነበር ፡፡

በእርግጠኝነት እናንተ ወይም እኔ በዚያን ጊዜ በዚያ የነበርን ቢሆን እና ይህንን አነጋገር ከእግዚአብሄር ሲመጣ ሰምተን ቢሆን ኖሮ በትክክል እንረዳውም ነበር ፡፡ ያንን ዛፍ መብላት.....እና ትሞታለህ! የሚለውን ደግሞም በእርግጥ ምን እንደተከሰተ ሁላችንም እናውቃለን ፡፡

አሳዛኝ የሆነው የዓለም ታሪክ፣አዳምና ሄዋን እግዚአብሔርን ያልታዘዙበትን ሀቅ ይመሰክራል ፡፡ እነርሱ ወዲያውኑ ከእግዚአብሄር እንዳይበሉ የተነገራቸውን ዛፍ በልተዋል ፡፡

*«ነገር ግን በገነት መካከል ካለው ከዛፉ ፍሬ፥ እግዚአብሔር አለ፡፡ እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ አትንኩትም፡፡ እባብም ለሴቲቱ አላት፡፡ ሞትን አትሞቱም፤ ከእርስዋ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ፡፡ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደ ሆነ፥ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ፥ ለጥበብም መልካም እንደ ሆነ አየች፤ ከፍሬውም ወሰደችና በላች፤ ለባልዋም ደግሞ ሰጠችው እርሱም ከእርስዋ ጋር በላ፡፡» (ዘፍጥረት 3፣3-6)*

አዳምና ሔዋን እግዚአብሄር ለእነርሱ የሰጣቸውን ብቸኛ ሕግ ተላለፉ፡፡ እነርሱ የተከለከለውን ዛፍ ፍሬ በሉ፡፡እናም እነርሱ በዚያኑ ቀን አልሞቱም ነበር፡፡በዘፍጥረት ምዕራፍ ሦስት ውስጥ የሚገኘውን መላውን የታሪክ ዝርዝር የምታነቡ ከሆናችሁ፣አዳምና ሚስቱ ሔዋን ከተከለከለው የዛፍ ፍሬ ከበሉ በኋላ ሲወድቁና ሲሞቱ አታገኟቸውም ፡፡ሀቅ በሆነው ሁኔታ፣ ሔዋን ልጆችን የወለደች ሲሆን፣ከነበሯትም ልጆች መካከል /አቤል/ የተባለው እንደተገደለና ከዚያም ተጨማሪ ልጆችንም የወለደች መሆኗን መጽሐፍቅዱስ ይናገራል፤ ይህም ሁሉ የሆነው የተከለከለውን የዛፍ ፍሬ ከበሉ በኋላ ነው ፡፡ እንዲሁም ደግሞ አዳም በመቶዎች ለሚቆጠሩ ዓመታት እንደኖረ እና ከዚያም በኋላ እስከ 930 ዓመታት ዕድሜው ድረስ እንዳልሞተ መጽሐፍቅዱስ ይናገራል ፡፡

«አዳምም ሴትን ከወለደ በኋላ የኖረው ሰባት መቶ ዓመት ሆነ፤ ወንዶችንም ሴቶችንም ወለደ፡፡

አዳምም የኖረበት ዘመን ሁሉ ዘጠኝ መቶ ሠላሳ ዓመት ሆነ፤ ሞተም፡፡ »(ዘፍጥረት 3፣3-4)

ነገር ግን አዳም የዛፉን ፍሬ ከበላ በኋላ በመቶዎች ለሚቆጠሩ ዓመታት ለመኖር የቻለው እንዴት ነው? በሆነ መንገድ እግዚአብሄር ተሳስቶ ነበር ለማለት ይቻላልን? እኛ እርሱ /እግዚአብሄር/ እንደሚዋሽ ለማሰብ እንኳን አንደፍረም ፡፡ አይደለም ፡፡ አለዚያም እነዚህ ነገሮች አማራጮች ናቸው ፤ እግዚአብሄር ፈጽሞ አይሳሳትም ደግሞም ለእርሱ ሀሰትን ለመናገር የማይቻል ነው ፡፡ እንግዲያውስ ይህንን እንዴት ልናብራራው እንችላለን? መልሱ እኛ መጽሐፍቅዱስን አንድ ጊዜ በመንፈሳዊ መረዳት ከተመለከትነው እይታ አንጻር ይመጣል ፡፡ እኛ ልንገነዘበው የሚገባን ነገር እግዚአብሔር እርሱ ሊያደርገው ያለውን ሞት በተናገረበት በመጀመሪው ቀን በሰው ልጆች ላይ ሊያመጣው የሚችል መሆኑን ነው፡፡ ነገር ግን በዚያ ቀን ሰው የሞተው ሞት አካላዊ ሞት ሳይሆን ከዚያ ይልቅ መንፈሳዊ ሞት ነበር ፡፡

«በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ፤ በእነርሱም»(ኤፌሶን2፣1)

«እናንተም በበደላችሁና ሥጋችሁን ባለመገረዝ ሙታን በሆናችሁ ጊዜ፥ ከእርሱ ጋር ሕይወትን ሰጣችሁ፡፡ በደላችሁን ሁሉ ይቅር አላችሁ፡፡»(ቆላስስ 2፣13)

ሰው በሐጢያቶቹ ምክንያት እንደሞተ በእነዚህ ጥቅሶች በኩል እንማራለን ፡፡ የሰው ልጅ በነፍሱ ህልውና የሞተ አንደሆነ መጽሐፍቅዱስ ይናገራል፡፡ እነርሱ በሐጢያት ከመውደቃቸው በፊት በአካልና በነፍስ በሁለቱም ሰው ህያው ነበር፡፡እርሱ ከእግዚአብሄር ጋር ህብረት ነበረው፡፡ በእግዚአብሔርና በሰው ልጅ መካከል የጠበቀ ግንኙነት ነበር ፡፡

ነገር ግን አንድ ጊዜ ሰው ሐጢያትን ሲደርግ ፣ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የነበረው ግንኙነት ተሰበረ ፡፡ እርሱ በዚያ የመጀመሪያ ቀን በነፍሱ ሞቷል፡፡ለዚያም ነው በመዳን ቀን ላይ እግዚአብሔር ሰዎችን በሚያድንበት ጊዜ ፣ለእነርሱ በነፍሳቸው ዳግመኛ ወደ መወለድ መምጣት አስፈላጊ የነበረው፡፡ መዳን ሙታን ለሆነው የሐጢያተኛው ነፍስ እንደገና መሰራት ነበር ፡፡

ለጥናታችን ጠቃሚ የሆነው ነጥብ፣ እግዚአብሔር በቀላሉ እንዲህ የተናገረው ነው ፤ ‹‹ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና ፡፡ ›› ያለው ፡፡ እግዚአብሄር ይህንን ሰው በምን ዓይነት ሞት እንደሚሞት ሳይለይ ተናግሯል፡፡ እርሱ እንደዚያ ሞት በሚልበት ጊዜ በነፍስ ይሁን እንዲሁም ደግሞ በአካላዊ ስጋ ይሁን በተሻለ ሁኔታ አልገለጠውም ፡፡

ስለዚህ በመጽሐፍቅዱስ ውስጥ የተመዘገበው የመጀመሪው ፍርድ በትክክል መንፈሳዊ ፍርድ እንደነበር እናያለን፤ያ መንፈሳዊ ነበር፣ምክንያቱም የአዳምና የሔዋን ነፍሶች በዚያ ቀን ሲሞቱ ማንም ሰው ለማየት አልቻለም ፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ፣ሰይጣን ለመናገር እንደቻለው እርሱ ትክክል ነበር እናም እርሱ‹‹ እዩ ፣እንደማትሞቱ ነገሬአችኋለሁ ፡፡ ተመልከቱ! በእናንተ ላይ ምንም ነገር አልሆነም ፡፡ እናንተ አሁንም በጣም በተሻለ ሁኔታ በአካል ህያዋን ናችሁ›› በማለት ተናግሯቸዋል ፡፡

ደግሞም ማንኛውም ውጫዊ ተመልካች ከእርሱ ጋር ይስማማል፡፡ አዎ፣እርግጥ ነው እግዚአብሔር ተናግሮት እንደነበርው ምንም ነገር አልሆነም ይላል፡፡ ይሁንና፣ያ አስተሳሰብ ሙሉ በሙሉ ስህተት ነው፡፡ አንድ ነገር ተከስቷል ፡፡ አንድ ነገር በጣም እውነት የሆነ ሲሆን እናም ምንም እንኳን በመንፈሳዊው ዓለም የሆነም ቢሆን አንድ በጣም አሳዛኝ ስራ ተከስቷል ፡፡ በእነርሱ ላይ የእግዚአብሄር ቁጣ ሞልቶ የነበር ሲሆን እናም እነርሱ በነፍሳቸው ህልውና ሞተዋል ፡፡

አንዳንድ ሰዎች ‹‹ እሺ ፣ መልካም እግዚአብሔር በአዳምና በሔዋን ላይ መንፈሳዊ ፍርድን አምጥቶ እንደነበር እንፈቅዳለን፤ነገርግን ያ ማለት እ.ኤ.አ. ግንቦት 21/2011 ዓ.ም. የፍርድ ቀን ነበር ማለት አይደለም ›› ይሉ ይሆናል ፡፡ አዎ ያ እውነት ነው፣ነገርግን አሁን እኛ እ.ኤ.አ. ግንቦት 21/2011 ዓ.ም የፍርዱ ቀን መጀመሪያ እንደነበር ለማረጋገጥ እሞከርን አይደለንም ፡፡ በአሁኑ ሰዓት በፊታችን ያለው ጥያቄ የሆነው ፤እግዚአብሄር የዓለምን የመጨረሻውን የፍርድ ቀን ለማስተላለፍ እንዲቻል በመንፈሳዊ መንገድ ለማምጣት እንደሚችል ያ የሚቻል ነውን? የሚለው ነው ፡፡ አንድ ጊዜ ለዚህ ጥያቄ መልስን እንሰጣለን፤ከዚያም ወደ ግንቦት 21/2011 ዓ.ም እ.ኤ.አ. የፍርድ ቀን እንደሆነ ወደሚጠቁሙት ነጥቦች ለመቀጠል መልካም የሆነ ስምምነት ወዳላቸው ድንቅ ወደ ሆኑ የመጽሐፍቅዱሳዊ ማረጋገጫዎች ለመነጋገር እንችላለን ፡፡

ለአሁኑ ሃሳብ ወደ መጽሐፍቅዱስ እንደገና እንመለስና መንፈሳዊውን ፍርድ በሚመለከት ተጨማሪ የሆነ አንዳች ነገር ለማግኘት የምንችል ከሆንን እንይ ፡፡

## የጽዋው ምሳሌ

መጽሐፍቅዱስ ዘወትር የጽዋን ምሳሌ በመጠቀም የእግዚአብሔርን ቁጣ ይጠቅሳል ፡፡

***«ወጥመድ በኀጥኣን ላይ ያዘንባል እሳትና ዲን ዐውሎ ነፋስም የጽዋቸው እድል ፈንታ ነው፡፡»*** (መዝሙር11፣6)

ከእሳትና ከዲን በተጓዳኝ እግዚአብሔር በክፍዎች ላይ ወጠመድን ለማዝነብ እቅዱ እንደሆነ አስታውሱ፡፡እናንተ ምናልባትም በአስፈሪው የፍርድ ቀን ባልዳኑት የሰው ልጆች ላይ እግዚአብሄር ቀጥተኛ የሆንን እሳትና ዲንን እንደሚያዘንብባቸው አስባችሁ ይሆናል፣ነገርግን ወጥመድ የሚለውስ? ያ ወጥመድ ነው ፡፡ አንድ ሰው በመላው ምድር ላይ ወጥመዶች ወይም ከሽቦ የተሰሩ መያዣዎች ከሰማይ እየተወረወሩ እንደሚሄዱ በእውነት ያምናልን? በእርግጥ አይደለም ፡፡ እግዚአብሔር ይህንን ‹‹ ወጥመድ›› የሚለውን ቃል በመላው ዓለም ላይ ለሚኖሩ ለሁሉም ያልዳኑ ሰዎች የሚሰጠውን የቁጣውን ጽዋ መንፈሳዊ እንደሚሆን መረዳት እንችል ዘንድ ይህንን ወጥመድ የሚለውን ቃል ጨምሮታል ፡፡ይህ ቀጥተኛ ሳይሆን ፣ ነገርግን መንፈሳዊ ፍርድ ነው፡፡ ለዚህም ነው መጽሐፍቅዱስ ደግሞ በፍጻሜው ጊዜ መላው ዓለም እንደሚጠመድ የሚናገረው፡፡

***«ነገር ግን ልባችሁ በመጠጥ ብዛትና በስካር ስለ ትዳርም በማሰብ እንዳይከብድ፥ ያ ቀንም በድንገት እንዳይመጣባችሁ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፤ በምድር ሁሉ ላይ በሚቀመጡ ሁሉ እንደ ወጥመድ ይደርስባቸዋልና፡፡*** » (ሉቃስ21፣34-35)

እ.ኤ.አ. በግንቦት21/2011 ዓ.ም ላይ ዓለም/ቤተክርስቲያንም ከእነርሱ ጎን በመሆን/ እንደተደሰቱ ሲሆን ደግሞም ምንም አልሆነም

በማለት በቁጣ ተናግረዋል ። በዚያ ጊዜ መጀመያ ላይ በምድር ሁሉ የሚኖሩትን ሰዎች፣(በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉትን እና በውጭ ያሉትን) ያልዳኑትን ሰዎች በሙሉ በወጥመዱ ውስጥ ያስገባቸው ሲሆን ጽዋውንም እንዲጠጡ መስጠትን ጀምሯል ፡፤

## 2ኛው መንፈሳዊ ፍርድ፤ክርስቶስ ከእግዚአብሔር የቁጣ ጽዋ ይጠጣል

መጽሐፍቅዱስ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ የእርሱን ህዝቦች ሐጢያቶች በራሱ ላይ እንዲወስድና፣እግዚአብሐርም ቁጣውን በክርስቶስ ላይ እንዲጨምረው፣በእነርሱም ቦታ በማድረግ እርሱን እንደቀጣው ይገልጣል ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የእርሱን የወደፊት የማስተሰረይ ስራ እንዴት የከበረ እንደሚሆን ለማሳየትና ለመግለጽ ይችል ዘንድ ወደ ሰው ዘር ውስጥ ገብቷል።በጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ የእግዚአብሐርን ቁጣ መቀበሉን ጀምሮ ሳለ ይህንንም መግለጫ እያደረገ ሳለ ፤

*«ጥቂትም ወደ ፊት እልፍ ብሎ በፊቱ ወደቀና ሲጸልይ። አባቴ፥ ቢቻልስ፥ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ፤ ነገር ግን አንተ እንደምትወድ ይሁን እንጂ እኔ እንደምወድ አይሁን አለ። ወደ ደቀ መዛሙርቱም መጣ፤ ተኝተውም አገኛቸውና ጴጥሮስን። እንዲሁም ከእኔ ጋር አንዲት ሰዓት እንኳ ልትተጉ አልቻላችሁምን? ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ፤ መንፈስስ ተዘጋጅታለች ሥጋ ግን ደካማ ነው አለው። ደግሞ ሁለተኛ ሄዶ ጸለየና። አባቴ፥ ይህች ጽዋ ሳልጠጣት ታልፍ ዘንድ የማይቻል እንደ ሆነ፥ ፈቃድህ ትሁን አለ።* »(ማቴዎስ 26፣39፤42) በማለት ተናግሯል ።

ኢየሱስ የእግዚአብሐርን የቁጣ ጽዋ ጠጥቷል ፤ ነገርግን ይህ ማለት ምን ማለት ነበር? እርሱን ለማጥፋት የሆነ የእሳት ብልጭታ ከሰማይ ወርዶ ነበርን? አይደለም ። እንደዚያ የሚመስል ነገር አልነበረም ። በትክክል፣በጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ የነበረ ማንኛውም የውጭ ተመልካች ሰው ያዘነውን እና የተጨነቀውን ኢየሱስን ብቻ አይቷል።ሌላ ምንም ነገር አልነበረም ። በአጠቃላይ የእግዚአብሐርን ቁጣ በውጫዊው አመላካቾች የሆኑ ነገሮች አልነበሩም ። በሌላ አነጋገር፣በጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ ሳለ ክርስቶስ የእግዚአብሐርን ቁጣ እየጠጣ የነበረው በአካላዊ ፍርድ ሳይሆን ነገርግን በመንፈሳዊ ፍርድ ነበር።ኢየሱስ በመንፈሳዊው ዓለም ውስጥ እየደረሰበት ከነበረው ቅጣት አንጻር በትልቁ ተሰቃይቷል ።

ይህ ማለት እንግዲህ፣አሁን ጠቃሚ የሆኑት ሁለቱ መጽሐፍቅዱሳዊ ፍርዶች፤በኤደን ገነት በአዳምና በሔዋን ላይ የሆነው ፍርድ፣እና በጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ በክርስቶስ ላይ የሆነው ፍርድ በባህሪያቸው ሙሉ በሙሉ መንፈሳዊ ነበሩ ። እነዚህ ሁለት ፍርዶች በራሳቸው የፍርዱ ቀን በመንፈሳዊ መንገድ እንደሚሆን የሚለውን አስተሳሰብ ለመደገፍ በቂ የሆነ ማረጋገጫዎችን ያቀርባሉ፤ ቢያንስ ቢያንስ እነዚህ መጽሐፍቅዱሳዊ የሆኑ ቀድም ሲል የተደረጉ ነገሮች መኖራቸው ልባዊ የሆነን አንድ የእግዚአብሔር ልጅ እነዚህ ነገሮች የሚቻሉ እውነቶች መሆናቸውን በታማኝነት እንዲመረምር ያስገድዱታል። የሚሰሙአቸውን ነገሮች በሚመለከት ከእግዚአብሄር ቃል መጥተው እንደሆነ በታማኝነት የሚመረመሩትን እንዚያን የቤሪያን ሰዎች መጽሐፍቅዱስ ይጠቅሳል ፤

***«ወዲያውም ወንድሞች ጳውሎስንና ሲላስን በሌሊት ወደ ቤርያ ሰደዱአቸው፥ በደረሱም ጊዜ ወደ አይሁድ ምኵራብ ገቡ፤እነዚህም በተሰሎንቄ ከሚኖሩት ይልቅ ልበ ሰፊዎች ነበሩና። ነገሩ እንደዚሁ ይሆንን? ብለው ዕለት ዕለት መጻሕፍትን እየመረመሩ ቃሉን በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉ።***
»(የሐዋሪያት ሥራ 17፣10-11)

የእግዚአብሐር ህዝቦች ከእግዚአብሐር ቃል የሆኑ መረጃዎችን እንዲያው እጃቸውን በማርገብገብ በቀላሉ ቸል ማለት ሳይሆን ፣ነገርግን ከዚያ ይልቅ በጥንቃቂ እንዲሰሙና ከዚም ከእግዚአብሄር ቃል በሰሙት እነዚህን ነገሮች እውነት እንደሆኑና እንዳልሆኑ ነገሮቹን መፈተሽ አለባቸው ።

## መጽሐፍቅዱስ ሌላ ዋና የሆነ መንፈሳዊ ፍርድ ያስተምራል

ነገርግን እነዚያ ሁለቱ የእግዚአብሐር ፍርዶች አጠቃላይ አይደሉም። ለእኛ ለመረዳት ሌላ ደግሞ ፍርድ አለ ፤እርሱም የእግዚአብሐር ፍርድ በአዲስ ኪዳን አብያተክርስቲያናት ላይ፤

***«ፍርድ ከእግዚአብሔር ቤት ተነሥቶ የሚጀመርበት ጊዜ ደርሶአልና፤ አስቀድሞም በእኛ የሚጀመር ከሆነ ለእግዚአብሔር ወንጌል የማይታዘዙ መጨረሻቸው ምን ይሆን?»(1ኛ ጴጥሮስ 4፣17)***

እግዚአብሐር ለእኛ በዓለም ውስጥ ባሉት ማህበረ ምዕመናን ላይ ለማሳለፍ የሚያመጣውን የእርሱን የመጨረሻውን ዘመን ቁጣውን የሚጠቁሙ በቃሉ ውስጥ ትልቅ መጠን ያላቸውን መረጃዎች ያቀርብልናል ። እርሱ ደግሞ በአብያተክርስቲያናት ውስጥ ባሉት እና በማህበረ ምዕመናኑ ላይ የሚጨምረውን ቁጣውን ለመሳል የጽዋውን ምሳሌነት ይጠቀማል ።

***«የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይለኛል። የዚህን ቍጣ የወይን ጠጅ ጽዋ ከእጄ ውሰድ አንተንም የምሰድድባቸውን አሕዛብን ሁሉ አጠጣቸው። ከምሰድድባቸውም ሰይፍ የተነሣ ይጠጣሉ ይወላገዱማል ያብዳሉም። ከእግዚአብሔርም እጅ ጽዋውን ወሰድሁ፥ እግዚአብሔርም እኔን የሰደደባቸውን አሕዛብ ሁሉ አጠጣኋቸው። ዛሬ እንደ ሆነው ሁሉ ባድማና መደነቂያ ማፍዋጫም እርግማንም አደርጋቸው ዘንድ ኢየሩሳሌምንና የይሁዳን ከተሞች ነገሥታትዋንም አለቆችዋንም አጠጣኋቸው። »(ኤርምስ 25፣15-18)***

እግዚአብሐር በመጀመሪያ ጽዋውን ለኢየሩሳሌም/የአብያተክርስቲያናት ምሳሌ ናት/ እና ከዚህም ለተቀሩት መንግስታት /ዓለምን ይጠቁማል/ ይጨምረዋል።

***«እነሆ፥ ስሜ የተጠራባትን ከተማ አስጨንቃት ዘንድ እጀምራለሁ፤ በውኑ እናንተ ያልተቀጣችሁ ትሆናላችሁን? በምድር በሚኖሩ ሁሉ ላይ ሰይፍን እጠራለሁና ያለ ቅጣት አትቀሩም፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።»(ኤርምስ 25፣29)***

በእግዚአብሐር ቸርነትና ጸጋ፣ቤተክርስቲያን ዘመን ማብቃቱን ለእኛ እርሱ ገልጾልናል ።

በአብተክርስቲያናት ላይ ፍርዱ እ.ኤ.አ. በ1988 ዓ.ም በሆነው ዓመት ላይ ጀምሯል ። በዚያ ጊዜ ላይ የእግዚአብሐር መንፈስ ከአዲስ ኪዳን ማህበረ ምዕመናን መካከል የለቀቀ ሲሆን እናም ወዲያውኑ የወንጌሉ ብርሃን በዓለም ከሚኖሩ አብያተ ክርስቲያናት ወጥቷል ። ይሁንና፣ መጽሐፍቅዱስ በዚህ ነጥብ ላይ የሚያስተምር ቢሆንም እንኳን፣የአዲስ ኪዳን አብያተክርስቲያናት በዚህ አስፈሪ እውነት ባለመረበሽ በዚያው ቀጥለዋል ።

በርካታ የሆኑ የእነርሱ መጋቢዎች/ፓስተሮች/ እና የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች በእነርሱ ላይ የሚሆነውን ፍርድ በሚመለከት ከመጽሐፍቅዱስ ትምህርቶች ቢሰሙም ፣ ነገርግን እነርሱ ይህንን ውድቅ ያደረጉት ሲሆን ደግሞም ሙሉ በሙሉ አንደማይመለካታቸው አድርገውታል። ነገርግን ፣እነርሱ እንደዚህ ያለውን እጅግ አስገራሚ የመጽሐፍቅዱስ ትምህርትና በተለይም እንደመቃብር ጥልቅ ሆነውን ነጥብ እንዴት ቸል ሊሉት ቻሉ?

እነርሱ ይህንን ምንም ነገር እንዳልሆነ አድርገው ቸል ማለትና ውድቅ ማድረግ ይችላሉ ምክንያቱም ይህ በመንፈሳዊው ዓለም ውስጥ የሚገኝ ፍርድ ነው ። የእግዚአብሐር መንፈስ በመካከላቸው እንደነበረበት ጊዜ በፍጹም ሊታይ የማይችል ሲሆን እንዲሁም ደግሞ እርሱ አንድ ጊዜ የተዋቸው በመሆኑ እንደገና ፈጽሞ ሊታይ አይችልም። በአሁኑ ጊዜ በዓለም ውስጥ ያሉትን አብያተክርስቲያናት የከበባቸው ጨለማ መንፈሳዊ ጨለማ ነው ። ይህ በአካላዊ ዓይኖች እይታ እና ተፈጥሮአዊ በሆነ መረዳት ሊመረመር አይቻልም ። ነገርግን የእግዚአብሄር ህዝቦች እግዚአብሄር በሰጣቸው መንፈሳዊ እይታና በመለየት ላይ በመመስረት እነዚህን ነገሮች ለመረዳት ይችላሉ ።

***«ብዙ ሰዎች ሰውነታቸውን ያጠራሉ ያነጡማል ይነጥሩማል፤ ክፉዎች ግን ክፋትን ያደርጋሉ፤ ክፉዎችም ሁሉ አያስተውሉም፥ ጥበበኞች ግን ያስተውላሉ።» (ዳንኤል 12፣10)***

ምንም እንኳን ይህ አጠቃላይ የሆነ እና መንፈሳዊ ፍርድ ቢሆንም የእግዚአብሄር ምርጦች በአብያተክርስቲያናት ላይ የሚሆነውን ፍርድ እውነትናትና አሳሳቢነት ይሰሙታል፤ ይረዱታልም ።

## ማጠቃለያ

አሁን ሦስት መጽሐፍቅዱሳዊ የሆኑ ፍርዶችን የመረመርን ሲሆን ፣ደግሞም ማራኪ የሆነ አንድ ነገር አግኝተናል።እነዚህ እያንዳንዳቸው ሦስቱም ፍርዶች በባህሪያቸው መንፈሳዊ ህልውናዎች እንደሆኑ ብቻ ሊገለጹ ይችላሉ።እናም እኛ አነስተኛ የሆኑ ፣የማይታወቁና ይልቁንም ግልጽ ያልሆኑትን ፍርዶች እየተናገርን ሳይሆን፣ነገርግን እጅግ ጠቃሚ የሆኑትን በመጽሐፍቅዱስ ውስጥ የተመዘገቡትን ሦስቱን ፍርዶች እየተናገርን ነው ። በኤደን ገነት ውስጥ በሰው ልጆች ከሆነው የእግዚአብሐር ፍርድ፣ወይም በጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ በክርስቶስ ላይ ከነበረው የእግዚአብሐር ፍርድ ፤ወይንም በታላቁ መከራ ወቅት በአዲስ ኪዳን የህብረት ቤተክርስቲያን ላይ ከሆነው የእግዚአብሐር ፍርድ የበለጠ ጠቃሚ ከሆነ ነገር ይልቅ በምን ነገር ላይ እንወያያለን?

ሀቅ በሆነ ሁኔታ ፣በመጽሐፍቅዱስ ውስጥ የሚገኝን አንድ ፍርድ ከእነዚህ ከሦስቱ የበለጠ አድርጎ ለመሰየም የማይቻል ነው ። ያም መጽሐፍቅዱስ መንፈሳዊ ፍርድን ያስተምራልን? ወደሚለው ወደ ዋናው ጥያቄያችን እንድንመለስ ይመራናል።መጽሐፍቅዱስን ከመረመርን በኋላ በእርግጠኝነት አዎ ያስተምራል በማለት ለመናገር እንችላለን።እግዚአብሐር መንፈሳዊ የሆነውን/ በስጋዊ ዓይን የማይታይን /ፍርድ በሰው ልጆች ላይ በሐጢአታቸው አንጻር እንደሚያመጣ መጽሐፍቅዱስ በእርግጥ ያንን ያስተምራል ፡፤

ነገርግን፣በዓለም በአጠቃላይ በአሁኑ ጊዜ ለእኛ ትልቅ ጥያቄ የሆነው፤እግዚአብሄር መንፈሳዊውን ፍርድ ለማስተላለፍ እ.ኤ.አ. በግንቦት 21/2011 ዓ.ም ጀምሮ አምጥቶታልን? የሚለው ነው። የመጽሐፍቅዱስ ምላሽ የሆነው፤አዎ፣ያ መንፈሳዊ ፍርድ በዚያ ቀን ላይ እንደጀመረና አሁን እስካለንበት ጊዜ ድረስ እየቀጠለ እንደሆነ ለመናገር የመጽሐፍቅዱስ ማረጋገጫዎች የሆኑ መልካም ስምምነቶች አሉ።

በእርግጥ፣እኛ በእውነተኛነት ራሳችንን ለመጠየቅ የሚያስፈልገን መጽሐፍቅዱሳዊ የሆነው ማስረጃ እጅግ ጠንካራ ነው ። ይህም እኛ ቀደም ሲል መንፈሳዊውን ፍርድ ፈጽሞ እንድንገነዘበው ይልቁንም ለመጨረሻው ፍርድ የሚቻል እንደሆነም እንኳን ያልተገነዘብነው ጉዳይ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ሆኖም ግን እግዚአብሔር አካላዊ እና በጣም ቀጥተኛ በሆነ ሁኔታ በምድር ህልውና የመጨረሻው ጊዜ ላይ ሁሉንም ነገር እንደሚደመስሰው መጽሐፍቅዱስ እንደሚያስተምር ማስታወስ አለብን ።

እኛ ሁላችን ከልብ በሆነ ሁኔታ በዚህ ጠቃሚ በሆነው የመጽሀፍቅዱስ ትምህርት እንስማማለን ። ነገርግን መጽሀፍቅዱስ ደግሞ እ.ኤ.አ. በግንቦት 21/2011 ዓ.ም የጀመረው ክፍለጊዜ በመንፈሳዊው መንገድ የሚታወቀው ‹‹የፍርዱ ቀን›› እንደሆነ ያስተምራል ።

ይህ መንፈሳዊ ፍርድ የተወሰነ ቁጥር ላላቸው ቀናት የሚቀጥል ሲሆን እናም በመጨረሻም፣በዚህ ክፍለ ጊዜ መጨረሻ ቀን ላይ የእግዚአብሐር ቁጣ አካላዊ በሆነ ሁኔታ ራሱን እንደሚገልጥና ይህንን መላውን ፍጥረት ካልዳኑት ሰዎች ጋር በአንድ ላይ ያጠፋቸዋል ። በአሁኑ ጊዜ ህያው ሆኖ የሚኖር ሰው ሁሉ በመጽሐፍቅዱስ ‹‹የፍርድ ቀን›› በማለት ከሚያስታውቀው ክፍለጊዜ ውስጥ እንዲገባ መጽሐፍቅዱስ ይገልጣል። በዚህ ጊዜ እኛ ሁላችን በፍርድ ቀን ውስጥ እየኖርን ነው። የሚከተለው የመጽሐፍቅዱስ ክፍል በከፋ ሁኔታ በመሟላት ላይ ነው ።

«በምድር ላይ የምትኖር ሆይ፥ ፍርሃትና ገደል ወጥመድም በአንተ ላይ አሉ።» (ኢሳይያስ 24፣17)

በእርግጥም ፣ይህ አስከፊ የሆነው እውነት የዚህን አሁን ያለንበትን ፍርድ ክፍለ ጊዜ ባህሪያት በሚመለከት በብዙ ጥያቄዎች ውስጥ ጥሎናል ።

እናም ደግሞ የእግዚአብሐር ምርጥ ህዝቦች አሁንም በዚህ ጊዜ ውስጥ በምድር ላይ ሊኖርና ሊቀሩ መቻላቸው እንዴት እንደሆነ እንደነቃለን ።

እነዚህ እና ሌሎችን ተጨማሪ ጥያቄዎች በሚቀጥለው የዚህ በራሪ ወረቀት/ትራክት/ ተከታታይ እትም ለመመለስ እንፈልጋለን።

### *ለተጨማሪ መረጃ ይጎብኙ*

www.ebiblefellowship.com
www.ebible2.com
Visit our Facebook page:
Also visit our YouTube Channel
www.facebook.com/ebiblefellowship
www.youtube.com/ebiblefellowship1
You may send a message, question comment to:
ebiblef ellowship@juno.write to us at: E Bible Fellowship,
Box 1393 Sharon Hill, PA 19079